# ዜና ኢሕአፓ

ዴሞክራሲያዊ / Democratic

በኢሕአፓ የፖለቲካና የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ
በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ የዜና መጽሔት

ቁጥር 1 ታኅሳስ 2000


## ርዕሰ አንቀፅ

## ምርጫው ፥ በነበረው ሁኔታ መቀጠል ወይም በለውጥ ድርጅታችንን ማስቀጠል

ርዕሰ አንቀፃችን ከመቅፅበት አንዳች ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም ብለን እንገምታለን:: **ለመሆኑ በኢሕአፓ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ምን ነበር?** የሚል:: ይህን መሰረታዊ ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ግን አንድ ጉዳይ ግልፅ ሊሆን ይገባል:: በጥቂት አምባገነኖችና ጭፍን ተከታዮቻቸው ተገፍተንም ቢሆን ከልጅነት እስከ ዕውቀት የፖለቲካ ትግልን አፈር ፈጭተን፥ ጭቃ አብኩተንና ውኃ ተራጭተን አብረናቸው ካደግን ጓዶቻችን ለጊዜውም ቢሆን ለመለየት መቁረጣችን በፍፁም አላስደሰተንም:: ዛሬም ቢሆን ዕቃ እንደረሳ ሰው ቅር ቅር ይለናል:: ከኒህ ሃቀኛ ጓዶቻችን የምንገናኝባቸውን አፋጣኝ መንገዶች ከማውጠንጠን ለአፍታም ቦዝነን አናውቅም:: ያለጥርጥር መቁረጥ ግን ነበረብን:: አፈሩን ያቅልልላቸውና እውቁ ፀሐፌ ተውኔትና ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድሕን ቀዌሳ ባንድ ወቅት ቁርጥ ውሳኔ የማድረግን አስፈላጊነት ሲያብራሩ:-

"የሰው ልጅ እምብዛም የሚሳነው ነገር የለም:: የሰብዓዊነት ቀና ውድድር ከያዘ እንደነጋንዲ እንደነጴጥሮስ ወደ ቅዱስነት ባሕል ይዘልቃል:: ጨረቃን በአክናፉ አልፎ ማርስ ላይ የወጣው እኮ ገና ዛሬ ነው:: ወደ ጭካኔ ባሕል ካሽቆለቆለም ደግሞ የሰው ልጅ እንደነሣጥናዔል ከአውሬ ይብሳል:: ከአውሬነት ጫካ ወጥቶ ጎጆ መቀለስ የጀመረው እኮ ገና ትላንትና ነው:: ስለዚህ የሰው ልጅ እምብዛም የሚሳነው ነገር የለም:: በፈቀደው አቅጣጫ እንዲዘልቅ እግዚአብሔር ችሎታውን ሰጥቶታል:: ጭካኔን ከፈቀደ ከነሄሮድስና ከነሣጥናዔል ብሶ ዛሬውኑ ይተራረዳል:: ቅንነትን ከፈቀደ ደግሞ አበው ባወረሱት የጋራ ባሕል ፀንቶና "ራሱን አውቆ" እንደቅዱሳን ዛሬውኑ ራዕይ ያያል:: ምርጫው የራሱ ነው" ብለዋል::

አዎን – እኛም መቁረጥ ነበረብን:: ስለሆነም ቆርጠናል:: ኢሕአፓን ዴሞክራሲያዊነት ለማላበስ ስንነሳም ከፊታችን የተደቀኑት በአምባገነናዊና በፀረ-ዴሞክራሲያዊ አሰራር መቀጠል ወይም አለመቀጠል የሚሉ ሁለት ተፃራሪ ምርጫዎች ብቻ ነበሩ – በነበረው ሁኔታ መቀጠል ወይም በለውጥ ድርጅታችንን ወደፊት ማስቀጠል::

ድርጅታችን ኢሕአፓ እንደዕድሜ ባለፀጋነቱ አያሌ በፖለቲካ ትግሉ መስክ 'ጥርሳቸውን የነቀሉ' የሚባሉ አባላት አፍርቷል:: እኒህ አባላት ድርጅቱ ባሳለፋቸው ውጣ ውረዶች አብረው የተሰቃዩና የተንገላቱ ሲሆኑ ክቡሩን የሕይወት መስዋዕትነት የከፈሉት ደግሞ ግንባር ቀደም ተጠቃሾች ናቸው:: እንዳውም ዛሬ በኢሕአፓ ውስጥ ለተደረገው መሰረታዊ ለውጥ መከሰት

ዋነኛ ምክንያት " የኒያ ፋና ወጊዎች ደም በከንቱ መቅረት የለበትም፤ መስዋዕትነትን በድፍረት የተቀበሉ የኒያ ዘላለማውያን ጀግኖች 'የታጋይ ድምፅ ይጮሃል!' ጥሪ ተገቢው ምላሽ ሊሰጠው ይገባል" የሚል ጀግኖቻችን ትተውልን ካለፉት የድፍረት ጥሪት የተቆነጠረ የቀጣይ ጥረት ውጤት ነው:: ዛሬ በኢሕአፓ ውስጥ ሊከሰት የቻለው ለውጥ "ተክቶን ታጋይ አልፏል፥ የኛም ትግል ይቀጥላል" የሚለው ለኒያ ቆራጥ ሰማዕታት ጓዶቻችን የገባነው ቃል ኪዳን ከነቢብ ወደገቢር መለወጥ ያለበት መሆኑ የግድ ያለውና የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ያስከተለው የለውጥ ሂደት ውጤት ነው:: ስለሆነም ነው መቁረጥ የነበረብን - ኢሕአፓም አመራሩም አሰራሩም መለወጥ አለበት ብለን በቁርጠኝነት የተነሳነው::

አምባገነኑ ቡድን በበኩሉ ተገቢውን ጥያቄያችንን በተገቢው መንገድ ከማስተናገድ ይልቅ "አሻፈረኝ፤ በነበረው አሰራር ብቻ ነው መቀጠል የሚቻለው፤ ካልበለዚያ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ'" ሲል በጋራ በተጠራ የአባላት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ በድፍረት ከመናገር ባሻገር ለውጥ ፈላጊውን ወገን ለማባረር የነበረውን ፍላጎት በገሃድ አሳይቷል:: በአንድ ድርጅት ውስጥ መዋቅርና እርከንን በጠበቀ ሁኔታ የተደረገን ውስጠ-ፓርቲ ትግል የጠላት፥ የሰርጎ ገቦች፥ የሲ. አይ. ኤ ቅጥረኞች፥ የወያኔዎች እያለ በማክቸልቸልም የፓርቲያችን የረጅም ዘመን የትግል ጓዶች መካከል ጥላቻና ቂም በርክቶ አለመተማመንና መፈራረጅ እንዲተረፈረፍ ምክንያት ሆኗል:: ይህም በድርጅታችን ታሪክ ፍፁም ይቅርታ የማያገኝና የማይሽር ጠባሳ ሆኖ ይኖራል:: ዛሬ ለውጥ አጋቹ ወገን ለፓርቲውም ለራሱም ሳይበጅ በነበረው አምባገነናዊና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊቱ ቀጥሎበታል:: ጥረታችን - የአመራር ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር እንዲያያዝ ለማስቻል ነበር - ምላሹ ግን "የፖለቲካ ፓርቲ የንግድ ኩባንያ አይደለም:: ተጠያቂነት ቀድሞ ያልነበረና የሌሎች አሰራር እንጂ የእኛ አይደለም" የሚል አሻፈረኝ የተሞላበት ሆነ:: ሙከራችን - በጠቅላላ ጉባዔ ያለምንም መበላለጥ በእኩል ደረጃ የተመረጡ የአመራር አባላት መካከል እምነትን ለማጎልበትና የሁሉንም እኩልነት ለማረጋገጥ የሚቻልበትን መንገድ ለመፍጠር ነበር ምላሹ ግን "የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኖ ተመረጠ ማለት ታማኝ ነው ማለት አይደለም" የሚል ትዕቢት የተሞላበት ሆነ:: ድካማችን - ተጨባጭ ተግባራዊና ሊለካ በሚችል የስራ እቅድ የሚራመድ አመራርን ለመምረጥ ነበር ምላሹ ግን የጉባዔ ውክልናን ሳይቀር ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር በማዋል ዳግም በአምባገነንነት ለመቀጠል ቁርጠኝነት የታየበትና በአደባባይ በግልፅ ማጭበርበር የተፈፀመበት ሆነ::

በአጠቃላይ ለውጥ ፈላጊው ክፍል በድርጅቱ ውስጥ አባላት የሃላፊነት ቦታ የሚይዙት ለተወሰኑ የአመራር አባላት በሚያሳዩት ወይም ባላቸው ታማኝነት ሳይሆን በብቃታቸው እንዲሆን ለማስቻል፥ እንዲሁም የአመራር አባላት፥

- ከድርጅቱ ሕግ በላይ እንዳይሆኑ መቆጣጠሪያ እንዲበጅ፥
- በአሰራር ሂደት የግልቃገብነት ሚና እንዳይጫወቱና በመካከላቸው የመከባበር መንፈስ እንዲሰፍን፥
- የገቡትን ቃል ኪዳን የሚጠብቁ ቃላቸውን አክባሪና ተግባራዊ አድራጊ እንዲሆኑ፥
- ለድርጅቱ ዕድገትም ሆነ ጥፋት ኃላፊነት ለመቀበል ዝግጁነት እንዲኖራቸው፥
- ስም አጥፊነት፥ ሰብዕና ገፋፊና አሳፋሪ አሉባልታ ከማሰራጨት የታቀቡ እንዲሆኑ፥
- ድርጅቱ የአዳዲስና የተለያዩ ሃሳቦች ማፍለቅን የሚያበረታታ ሆኖ ታሪካዊ ቦታውን መልሶ እንዲያገኝ ለማስቻል የሚደረጉ ጥረቶችን የሚያግዝ እንጂ የሚያጥላላ ወይም ጨርሶ የማይቀበል እንዳይሆን፥በጠቅላላው ከኢሕአፓ መሰረታዊ መተክሎች በራቀና በተፃረረ

በከብት በሽታ ተጠቅተውበት ስለነበር ከእገታው ጋር ተዳምሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ሆኖበታል።
በሌላ በኩል የተባበሩት መንግስታት ያካባቢውን ነዋሪዎች ሁኔታ ለመመርመር አንድ ኮሚሽን ባለፈው መስከረም ማቋቋሙ ሲታወቅ ገለልተኛ የሆነው ይህ ኮሚሽን ለአንድ ሳምንት በዞኑ ዋና ከተማ በጅጅጋ፣ እንዲሁም በደገሃቡር፣ በቀብሪ ደሃር ጎዴና ሌሎች ከአስር በሚበልጡ ትንንሽ የገጠር ከተሞች እየተዘዋወረ ጎብኝቶ ነዋሪውን አነጋግሯል። የደረሰበት መደምደሚያም በሕወኃትና በ"ነፃ አውጪው ድርጅት" መካከል በተፈጠረው ቁርቋሶ ያካባቢው ሕዝብ በእጅጉ እንደተጎዳ በአሃዝ በተደገፈ ማስረጃ አሳይቷል። በተለይ ህወሓት የፈጠረው ሽብር ባስቸኳይ ካልቆመ አብዛኛው ያካባቢው ነዋሪ ሕዝብ የረሃብና የበሽታ ሰለባ እንደሚሆንም አስጠንቅቋል።
በኦጋዴን የተከሰተው ይህ የሰብዓዊ መብት ረገጣ በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ከሚደረገው ተለይቶ የማይታይ ቢሆንም ህወሓት በአምባገነን ባሕሪው የኢትዮጵያውያንን ሁሉ ችግሮች ይበልጥ እያባባሰና እያቆላለፈ መሄዱ ተደጋግሞ የታየ ሃቅ ነው።

(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፣ ከሐረር)

## ከማያቋርጡ የኢሕአዴግ ቀልዶች - የብሔሮች ቀን በዓል

እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር ዲሴምበር ዘጠኝ 2007 ኢትዮጵያ ውስጥ 'የብሔሮች በዓል' ተከብሯል ተብሎ ዜናው ከተሰራጨ ሰነበተ። በበዓሉ ላይም የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች ቀደም ሲል በደርግ ጊዜ ይደረግ እንደነበረው በማዘገዣ በባሕል ልብሶቻቸው አጊጠውና ተንቆጥቁጠው የየባሕላቸውን ጭፈራና ዜማ እንዲያሰሙ ተደርጓል። የኢሕአዴግ ቱባ ቱባ ባለስልጣናትም የተለመደውን የሚያሰለችና እጅ እጅ የሚል ዲስኩራቸውን አሰምተዋል።

በተለይ ባሁኑ ወቅት የዚህን በዓል ትክክለኛ ትርጓሜ መመርመር የግድ ይላል። ኢሕአዴግ በጣም ከሚኩራራባቸውና በታሪክም ወደፊት የምመሰገንባቸው ብሎ ሰርክ ከሚመፃደቅባቸው ጉዳዮች አንዱ የብሔር/ብሔረሰቦችን መብትና እኩልነት አስከብሬያለሁ ብሎ በፅኑ ማመኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የዚህ ጉራ ተጋሪ አይደለም። አገዛዙ በገዛ ራሱ ሕገ-መንግስት ላይ ያሰፈረውን አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝን እንኳ ብንመለከት ያገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና የኢሕአዴግ ፖሊሲ ጨርሶ የማይገናኙ መሆናቸውን ነው የሚያመለክተው። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙዎች ብሔረሰቦች ተሰጠ የተባለውን መብት ተግባራዊ ሲያደርጉ ይታሰራሉ፣ ይሰደዳሉ፣ ይገደላሉም።
ነጋ ጠባ የኢሕአዴግ መገናኛ ብዙሃን እንደሚያላዝኑት አምባገነኑና አሸባሪው አገዛዝ የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች ስምምነት የሚሻ ሳይሆን በመካከላቸው ጥርጣሬና ግጭትን የፈጠረና ዛሬም ድረስ የሚፈጥር ነው። ገና ከጅምሩ ለስልጣን ሲታደል በኢትዮጵያ ታሪክ ለተፈጠረው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ ያደረገው አንድን ብሔር ነው። ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች÷ ነፃው ፕሬስና የብዙሃን ማሕበራት ባደረጉት ትግልና ማስተባበል ነው እንጂ እንደኢሕአዴግ ዓላማ ቢሆን ኖሮ የሃገሪቱ ብሔረሰቦች እርስ በርስ እስከመጠፋፋት በደረሱ ነበር። የህዝቦቿ አርቆ አስተዋይነትና ለረጅም ዘመናት በመከባበርና በመፈቃቀር በጋራ አብሮ የመኖር የቆየ ባሕል በቶሎ የማይደፈርስ በመሆኑ እንጂ እንደአገዛዙ ጭፍን አመለካከትና እርምጃ ቢሆን ኖሮማ ዛሬ ኢትዮጵያ ለከፍተኛ አደጋ በተጋለጠች ነበር።
ኢሕአዴግ ለስልጣን ከበቃበት ጊዜ ጀምሮ በኦሮምያ በአማራ በሲዳማ በቤኒሻንጉል በኑወር በጋምቤላና ለሎችም አካባቢ ሕዝቦች ላይ ያደረሰው እልቂት ተዘንግቶ የብሔሮች በዓል የሚሉ አነጋገር እንዲያው ቧልትና ቀልድ ነው።

በቤኒሻንጉልና በጋምቤላ አካባቢዎች ከዚህ በፊት ሆኖ በማያውቅ መንገድ በአካባቢው ነዋሪዎች መካከል መለስተኛ ግጭቶች ሲነሱ ይበልጥ በማጋጋልና ወደማይታረቅ ቅራኔ ሆን ብሎ በመግፋት ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ቂም በቀል በማስፋፋት ተግባር በቀጥታ የተሳተፈው ራሱ ኢሕአዴግ መሆኑ ከቶውንም አይዘነጋም። የኑወርና የአኘዋክ ብሔረሰቦችን በማጋጨት የፈፀመው ጭፍጨፋ ዜጎቹን በስደት ወደ ሱዳን እንዲሻገሩ ማስገደዱንና ታዛቢዎች በማስረጃ እንዳረጋገጡት የኢሕአዴግ ወታደሮች ራሳቸው ነዋሪውን በገዛ ቀዬው እያሳደዱ በመግደልና ሴቶችን በመድፈር አስነዋሪ ተግባር መሰማራታቸው ተዘግቧል። በተመሳሳይ ሁኔታ አንዴ ከጉሙዞች ጋር የቆመ እየመሰለ ቤኒሻንጉሎችን ሲያጠቃ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከቤኒሻንጉሎች ጋር ያበረ እየመሰለ "መጤ" የሚላቸውን ሺናሻዎችን ሲያጠቃና እርስ በርስ በማጨራረስ ተግባር በይፋ መሰማራቱ በተጨባጭ መረጃ የተረጋገጠ እውነት ነው። በኦሮምያ ክልልም እንዲሁ አነግ ተደማጭነት ሊያገኝ ይችላል ብሎ በሚፈራባቸው ቦታዎች ሕፃናትን ወጣቶችንና አዛውንቶችን ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በእስርና በእንግልት እየቀጣ የሚገኘው ራሱ ኢሕአዴግ ነው። ተለጣፊ ፓርቲውን ኦሆዴድን ያልተቀበሉትን በሺህ የሚቆጠሩ ያካባቢውን ዜጎች በእስር እያማቀቀ መገኘቱም በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። እንግዲህ ይህ አገዛዝ ነው "የብሔሮች በዓል" አከበርኩ እያለ የሚያላግጠው። የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች በሰላምና በብልፅግና የሚኖሩት የዲሞክራሲ መብቶቻቸው ተከብረው ባሕሎቻቸውና ቋንቋዎቻቸው ዳብረው የአገሪቱም የሕዝቦቿም ልዕልናና አንድነት ሲከበር ብቻ ነው።

(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፣ ከአዲስ አበባ)

# ከሠፈሮ ሃገር

## የደቡብ አፍሪካው ኤ. ኤን. ሲ. ፓርቲ – የሰሞኑ ትርምስ

እንደሚታወቀው የደቡብ አፍሪካውን ዘረኛ አገዛዝ (አፓርታይድ) ገርስሶ የጣለው ከተመሰረተ አንድ ምዕተ ዓመት ለማስቆጠር ብዙ ያልቀረውና በተራማጅነቱ የታወቀው የኤ. ኤን. ሲ. (የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ) ፓርቲ ነው። አገሪቱ ከጥቂት ነጮች አስከፊ አገዛዝ ነፃ ከወጣች በኋላ የመጀመሪያው ፕሬዘዳንት የነበሩትና በፈቃዳቸው ስልጣናቸውን የለቀቁት አዛውንቱ ኔልሰን ማንዴላ ሲሆኑ እሳቸውን ተክተው ለዘጠኝ ዓመታት በሁለት ዙር ምርጫ አገሪቱን በማስተዳደር ላይ ያሉት ያገሪቱ ፕሬዘዳንትና የፓርቲው ሊቀመንበር ታቦ እምቤኪ ናቸው። ኤ. ኤን. ሲ. ምንም እንኳ ባለጥሩ ታሪክ የፖለቲካ ፓርቲ ቢሆንም በውስጡ ሁከትና መታመስ መከሰት የጀመረው ከሶስት ዓመታት ወዲህ ነው። ድርጅቱ ለስልጣን ከበቃ አስር ዓመታት የተቆጠሩ ቢሆንም አብዛኞቹ ያገሪቱ ሕዝቦች ከድህነት ለመላቀቅ አለመቻላቸው ለሁከቱ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል። በሃገሪቱ የጥቁር ከበርቴ መደብ ቢፈጠርም ሰፊውና ብዙሃኑ ድሃ ጥቁር ሕዝብ ግን የዕለት ጉርሱን እንኳ በበቂ ለማግኘት አለመቻሉ በኤ.ኤን.ሲ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እንዲኖር ዋነኛ ምክንያት ሆኗል። ይህም እያደገ መጥቶ በፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባላት መካከልም ልዩነቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። በሌላ በኩል የፓርቲው ምክትል ሊቀመንበር የነበሩት ያዕቆብ ዙማ ከሁለት ዓመት በፊት በሁለት ጉዳዮች ምክንያት ክስ ተመስርቶባቸው እንደነበር አይዘነጋም።

የመጀመሪያው ክስ የቤተሰባቸው ወዳጅ የነበረችና የኤድስ ሰለባ የሆነች አንዲት ነጭ ሴት በማስገደድ ደፍረዋል በመባል ሲሆን ሁለተኛው ክስ ደግሞ ከፈረንሳይ የመሳሪያ ድለላ ኩባንያ ጋር በመመሳጠር ብዙ ገንዘብ ከሽሪኮቻቸው ጋር ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ አግኝተዋል የሚል ነው።

የክሱ ክብደትና እውነትነት ገና በፍርድ ቤት የሚታይ ቢሆንም የፓርቲው ሊቀመንበርና ያገሪቱ ፕሬዘዳንት ታቦ እምቤኪ በሕጉ መሰረት ያዕቆብ ዙማን ከምክትል ሊቀመንበርነታቸው ቦታ ካነሷቸው ሰንብቷል። ይህ ድርጊት ግን የዙማን ደጋፊዎችና በእምቤኪ አገዛዝ ያልተደሰቱትን ሁሉ ባንድ ግንባር አሰባሰባቸው። በዚህ ጉዳይና ፓርቲው እምብዛም ለድሆች ምንም አለፈየደም በሚለው ዙሪያ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በፓርቲው ውስጥ ከፍተኛ ልዩነቶች መታየት ጀምረው ነበር።
ይህ በእንዲህ እንዳለ ኤ. ኤን. ሲ. ከሰራተኛው ማህበርና ከደቡብ አፍሪካ የኮምኒስት ፓርቲ ጋር የሶስትዮሽ የቆየ የጋራ ግንባር ቢኖረውም ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ግን ሁለቱም ክፍሎች በታቦ እምቤኪ አስተዳደር ላይ ያላቋረጠ ሂስ ማሰማት መጀመራቸውም በፓርቲው ውስጥ የነበረው ትርምስ ላይ የበኩሉን አሉታዊ ሚና ተጫውቷል። እነዚህና ሌሎችም ምክንያቶች ተደምረው ነው የዙማ ከሃላፊነት መነሳት በፓርቲው ውስጥ የነበረን ውስጠ ፓርቲ ትርምስ የበለጠ ያቀጣጠለው።
ይህም ተባብሶ ፓርቲው በታህሳስ ወር 2007 ፖሎክወይን በተባለች ከተማ ጉባዔውን ባደረገበት ወቅት ልዩ ሁኔታ ተፈጠረ። ታቦ እምቤኪ የፓርቲውን ሊቀመንበርነት ሊያጡ እንደሚችሉ ቢገመትም ዙማ ሳይጠበቅ ስድሳ በመቶ የሆነውን የፓርቲ ልዑካን ድምፅ በማግኘት ለድል በቁ። ከ3854 ድምፅ 2329 ዙማ ሲያገኙ ታቦ 1505 ድምፅ ብቻ ነበር ያገኙትና የተሸነፉት። ከዘጠኝ ክፍላተ ሃገራት ዙማ አምስቱን ሲያሸንፉ የሴቶችንና የወጣቶችን ማሕበራት ድጋፍም አግኝተዋል። በሌላ በኩል የጉባዔው አካሄድ ጭምር የፓርቲውን ሕግ የተከተለ አለመሆኑም ቀደም ሲል የነበረውን ትርምስ ይፋ ያወጣ ጉዳይ ሆኗል። እምቤኪ ንግግር እያደረጉ የተቋረጡበት በተለይም የዙማ ደጋፊዎች በመዝሙርና በጩኸት ስብሰባውን ያወኩበትም ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ሁኔታ መከሰቱም የወደፊቱን የፓርቲውን አንድነት ሊፈታተን እንደሚችል ታዛቢዎች ገምተዋል። በደቡብ አፍሪካ ሕግ መሰረት

ምንም እንኳ የፓርቲው ሊቀመንበር ያገሪቱዋም ፕሬዘዳንት መሆን ቢችል ዙማ ምንም እንኳ ሴት አስገድዶ ከመድፈር ክስ ቢያመልጡም ከሙስናው ክስ ካልፀዱ በስተቀር ከፕሬዘዳንትነት ሊታገዱ ይችላሉ። ግራም ነፈሰ ቀኝ፤ ኤ. ኤን. ሲ. ከእንግዲህ ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ ሊወድቅ እንደሚችል የፖለቲካ ተንታኞች ሁሉ ግምት ሆኗል።

(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፤ ከጆሓንስበርግ)

## ቬንዙዌላ

ቬንዙዌላ በላቲን አሜሪካ ክፍለ ዓለም የምትገኝና በነዳጅ ሃብት የታወቀች አገር ነች። አገሪቱዋ ዛሬ የምትታወቀው በነዳጅ

ሃብት ብቻም አይደለም። በመሪዋ በሂዩጎ ሻቬዝ ጭምር ነው። ሻቬዝ የአየር ወለድ ኮለኔል በነበረበት ወቅት እ. አ. አ. በ1992 መፈንቅለ መንግስት ሞክሮ ከከሸፈበት በኋላ በእስር ላይ ቆይቶ ነበር። ከእስር ከተፈታ በኋላ ግን በሕጋዊ ምርጫ ሁለት ጊዜ ተወዳድሮ አሸንፎ እነሆ ስልጣን ላይ ከቆየ ዘጠኝ ዓመት አለፈው።

ሻቬዝ በአገሩ በቬንዙዌላ የሚከተለውን ፖሊሲ "የሃያ እንደኛው ክፍለ ዘመን

ሶሻሊዝም" ይለዋል:: እንደሻቬዝ አባባል ከሆነ መንግስት ለድሆች ተጨናቂ ነው፤ የተለያዩ ተራማጅ እርምጃዎችን እየወሰደ ድሆች በቂ ምግብ እንዲያገኙ፤ ንፁህ ውኃ እንዲጠጡ፤ በሽምግልና ጊዜያቸው በቂ ሕክምናና እንክብካቤ እንዲያገኙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል ባይ ነው:: በሌላ በኩል ላለፉት ጥቂት ዓመታት የነዳጅ ዋጋ ጣራ መንካቱ አልከፋም:: ለሚያስፈልገው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ወጭዎች የነዳጅ ዘይት ፈሰስ እጅጉን አግዞታል:: ይህ የመንግስት ፖሊሲ ግን ጨርሶ በአገሪቱ ሃብታሞችና ቱጃሮች ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም:: ሃብታሞቹ (ብዙ ጊዜም ፀረ-ተራማጅ የሆኑ የምዕራብ አገሮችን ድጋፍ ይዘው) ለሻቬዝ መንግስት እንቅፋት ሆነዋል:: ያሏቸውን የግል መገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች እየተጠቀሙም ትግሉንና የአገሪቱን መሪ ያንቋሽሻሉ፤ ደጋግመው ፀረ-መንግስት ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋሉ::

እ. ኤ. አ. በ2002 ደግሞ ከበርቴዎቹ በሻቬዝ ላይ ለጥቂት ሰዓታት የቆየ መፈንቅለ መንግስት አድርገው ነበር:: በዚህም ተግባራቸው ላይ የአሜሪካ እጅ አለበት ተብሎ ይታማል:: ወታደሩ ግን ከሻቬዝ ጋር በመቆሙ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራው በቀላሉ ሊከሽፍ ችሏል:: ሌላው ከበርቴዎቹን ፀጉር የሚስነጭ ጉዳይ ቬንዙዌላ ከኩባ መንግስት ጋር ያላት ጤናማ የዲፕሎማቲክና የተራድዖ ግንኙነት ነው::

አገሪቱ ከብዙዎች የላቲን አሜሪካ አገሮች ጋርም ጥሩ ግንኙትነት አላት:: በተለይ የነዳጅ ዘይትን ረከስ ባለ ዋጋ በማቅረብም ትረዳለች:: ይህ እርዳታ በአሜሪካም በተወሰኑ ግዛቶች ውስጥ ለሚኖሩ በተለይም ድሆች ለሆኑት የሚለገስ ነው:: አልፎ አልፎም ከአሜሪካ አስተዳዳር በተለይም ከፕሬዘዳንት ቡሽ ጋር የተካረረ ፀብ ስላላቸው ቬንዙዌላ ፀረ- አሜሪካ ከሆኑ አገሮች ለምሳሌ ኢራን ጋር የጠበቀ ወዳጅነት አላት::

ቬንዙዌላ እ. ኤ. አ. በ2007 ላይ ዳግም የዓለም አቀፍ ዜና ዓቢይ ርዕስ ሆናለች::

ሻቬዝ ሶሽያሊዝምን ለማጠንከር ይረዳል በሚል ሕገ መንግስቱ የገደበበትን ዳግም ለፕሬዘዳንትነት የመመረጥ ዕድል ለመለወጥ ውሳኔ-ሕዝብ (ሬፈረንደም) እንዲደረግ አድርጎ ነበር:: በውሳኔ-ሕዝቡ ግን አርባ ዘጠኝ ለሃምሳ አንድ በሆነ ድምፅ የሻቬዝ ድምፅ ተሸናፊ ሆነ:: ሻቬዝን የዕድሜ ልክ ፕሬዘዳንት ማድረግ በውሳኔ-ሕዝብ መውደቁም ለዴሞክራሲ ታላቅ ድል ሆነ:: ሻቬዝ ወደአምባገነንነት የሚሄድበትን መንገድ ይጠርግ የነበረበት ሂደት ነውና የተሸነፈው:: በዚህም የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሶሺያሊዝም ገና ሳናጣጥመው እንደሃያኛው ክፍለዘመን ሶሺያሊዝም በአምባገነኖች ከመጠለፍ ዳነ:: የሚያሳዝነው ግን ሌሎች ተራማጅ ህጎች ከዚሁ ጋር ተዳብለው ለውሳኔ-ሕዝብ ቀርበው ኖሮ "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" ሆኖ እንዳያልፉ ሆነና ጉዳቱ ለህዝቡ ሆነ:: ሻቬዝም በምዕራባውያን ሃገሮች በተለይም በቡሽ አስተዳደር አሁንም ባይነቁራኛ እየተጠበቀ ነው::

(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፤ ከሰሜን አሜሪካ)

## ለታሪክ ለትውስታ

- ሰኞ ኦክቶበር 29 2007 የኢሕአፓ አስቸኳይ ጉባዔ ተካሄደ:: አዲስ ድርጅታዊ መዋቅርና አዲስ የአመራር ካውንስልም ተመረጠ:: ስለሂደቱም በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙኃን ድርጅታዊ መግለጫ ወጣ::
- ማክሰኞ ኦክቶበር 30 2007 አዲሱ የአመራር ካውንስል የመጀመሪያውን ፕሌነም (ስብሰባ) አካሄደ:: የአመራር ካውንስሉ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎችን ከመመስረቱም በላይ ሃላፊዎች በመመደብ ወደ ተግባር ተሰማራ::
- ረቡዕ ኖቬምበር 7 2007 "ቅድሚያ ሃገርና ህዝብ ለማዳን" በሚል ርዕስ የተዘጋጀው የዴሞክራሲያ ልዩ ዕትም ይፋ ሆነ::

- አርብ ኖቬምበር 16 2007 ዴሞክራሲያዊ ኢሕአፓ የተሰኘ የአባላት የውስጥ መድረክ ተከፈተ፡፡
- ቅዳሜ ኖቬምበር 17 2007 'የኢትዮጵያውያን ድምፅ መስተናገጃ የሆነው የዴሞክራሲ አዳራሽ VOICE OF ETHIOPIAN DEMOCRATIC ROOM (VEDR) ታዳሚዎችን ለማስተናገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ክፍት ሆነ፡፡

## ዓላማችንና ራዕያችን

**የኢሕአፓ ዋነኛ ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት፥ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝብና የሃገር አንድነት የሚጠበቅበት፥ የእምነትና የሃሳብ ነፃነት የሚከበርበት፥ በሕዝብ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሚቋቋም ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን መመስረት ነው፡፡**

(የኢሕአፓ ፕሮግራም ገፅ 2 1998ዓ. ም. )

ትግል ከራስ እንዲሉም በቅድሚያ፡-

1ኛ. ድርጅታችን ዛሬ በምንገኝበት ወሳኝ የታሪክ ወቅት ግንባር ቀደም ሆኖ ባሁኑ ወቅት በሃገራችን የተፈጠረውን የጠንካራ ድርጅት አመራር ክፍተት የመሙላት ብቃት ያለው የፖለቲካ ድርጅት እንዲሆን፥
2ኛ. የድርጅቱን ሕገ ፓርቲና ውስጠ ደንብ ተከትሎ በተግባር የሚንቀሳቀስ እንዲሁም ሰርቶ የሚያሰራ ጠንካራ አመራር እንዲኖረው፥
3ኛ. የድርጅቱ አባላት ሁሉ እምነታቸውንና ፍላጎታቸውን ሳይደብቁ በሙሉ ነፃነት የአዳዲስ አስተሳሰቦች ጭምር አፍላቂ በመሆን ድርጅታቸውንና የሚታገሉለትን ሕዝብ በብቃት እንዲያገለግሉ ለማስቻል የሚያበቁ ቀዳሚ ሁኔታዎችንና መደላድሎችን ጥቅምት 17 2000 ዓ. ም. በተደረገው ታሪካዊ ጉባዔያችን ላይ ፈጥረናል፡፡

### ከዘገምተኝነትና ከአምባገነን አሰራሮች ፍፁም የፀዳው የድርጅታችን የ ኢ ሕ አ ፓ ራዕዮች፡-

1ኛ. ኢሕአፓ ከምስረታው ጀምሮ የቆመላቸውን ዋነኛ መተክሎቹንና መታወቂያው የሆኑትን ስነምግባሮቹን ማለትም የዓላማ ፅናትን፥ ቁርጠኝነትን፥ ሃቀኝነትንና ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን መሰረት ባደረገ የተባበረ ሕዝባዊ ትግል ሕዝባችንን ለድል ማብቃት፥

2ኛ. የአርሶ አደሩን የሰራተኛውን የምሁሩንና የጠቅላላውን ሕዝብ ተሳትፎና የቁሳቁስ የጉልበትና የአዕምሮ ውጤቶች በመጠቀም ሕዝባዊ ትግሉን ማፋፋምና ማስፋፋት፥

3ኛ. ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበት ዴሞክራሲያዊ አሰራርን በድርጅቱና በሕዝቡ ውስጥ ማስረፅ፥

4ኛ. ኢሕአፓን እንደቀድሞው ሁሉ መልሶ የአርሶ አደሩ፥ የሰራተኛው፥ የወጣቱ የአዛውንቱ፥ የምሁሩ ባጠቃላይ የሰፊው ሕዝብ በማድረግ በቅርብ አብሮ መታገልና ማታገል፥

5ኛ. በድርጅቱ የእስከዛሬ የትግል ታሪክ አብረው ለተጓዙ ታጋዮችና ደጋፊዎች እንዲሁም ሃገር ወዳዶች መገናኛ ድልድይ የመሆን ዝግጁነት ማሳየት፥ መተግበርና በዚህም ሳቢያ፥

6ኛ. የሕዝብን ሙሉ እምነት መልሶ ለማግኘት ያላሰለሰና የማይቋረጥ ጥረት በማድረግ፥

7ኛ. አሸባሪውን አምባገነኑንና ዘረኛውን የሕወኃት አገዛዝ በተባበረ ሕዝባዊ ትግል አስወግዶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሚገባው ሙሉ የስልጣን ባለቤትነት ማብቃት ናቸው፡፡

## ከዴሞክራሲያ ማኅደር

" ኢሕአፓ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለአንዴም ለሁሌም የመገንጠልን አማራጭነት ውድቅ አድርገው የዴሞክራሲያዊ አንድነትን አማራጭ-የለሽነት እንዲቀበሉና ለዚህም ተባብረው እንዲታገሉ ጥሪ ያደርጋል:: ኢትዮጵያዊነት ደግሞ የሁሉም ትግልና መስዋዕትነት ውጤት በመሆኑ ማንም ቢሆን ማን ይህንን መለያውን ሊቀማ ካለመቻሉ ሌላ ሊጠራጠረውም የሚገባ ጉዳይ አለመሆኑም ሊታመንበት ይገባል:: የብሔረሰቦች ወግ፤ ባህል፤ ታሪክና ቋንቋዎች ተከብረው ለሀገራዊ አንድነታችን ጠቃሚ የሆኑ ቅርሶቻችንና-እሴቶቻችን መሆናቸውም ታምኖበት ሁላችንንም በእኩልነት ያቀፈች ታላቅ ሀገርን፤ የሁሉም ሕዝብዋ የጋራ የሆነች ሀገርን በጋራ ልናጠናክር እንችላለን ብሎ ኢሕአፓ ያምናል:: ለዚህም ልክ እንደ በፊቱ ይህንን ቅዱስ ዓላማችንን ከሚፃረሩ ፅንፎች መራቅና በተከሰቱበትም መታገል ይኖርብናል:: ለእኩልነትና ለመብት መከበር መቆም ተገቢና ፍትሀዊ ነው:: ለሀገራችን ለኢትዮጵያ በጋራ መታገልና ዜግነታችንንም ማስረገጥ ደግሞ ግዳጃችን ነው:: በዚህ መልክ ሲታይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት በዴሞክራሲ ለም ማሳ ላይ ጸድቆ እውን እንዲሆን በመታገል የወያኔን ዘረኛና ከፋፋይ አገዛዝ ማስወገድ የሁላችንም ተቀዳሚና ዋና ተልዕኮ ሊሆን ይገባዋል ሲል ኢሕአፓ ያሳስባል::"

<u>ከዴሞ፥ ኢሕአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ፥ ግንቦት 1994 ዓ.ም. ልዩ ዕትም፥ የተቀነጨበ</u>

"ትናንትም ዛሬም ወደፊትም ዋናው ቁምነገር የአገራችንና የህዝባችን ደህንነት ነው:: የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት ብዙ ምርጫ የላቸውም ፥ ተባብሮ ከመታገል ሌላ:: በዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ለድል የበቃው ኢሕአፓ በቅርቡ ባደረገው ጉባዔ የአወቃቀርና የአሰራር ማሻሻያዎች አድርጎና ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለው አመራር መርጦ ለሕዝብ የገባውን ቃልኪዳን እንደገና በማደስ በአዲስ መንፈስ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን ያካተተ ሁሉን አቀፍ የድርጅቶች ኅብረት እንዲመሰረት የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት ቆርጦ ተነስቷል:: በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት አባል ድርጅቶችና ለሌሎች ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ የጋራ የትግል ጥሪውን ያቀርባል:: ጥሪውም ትግሉም የሕወኃትን ጎሳዊ አገዛዝና ፖለቲካን አሽቀንጥሮ ለመጣል እንዲሁም በኢትዮጵያ ግዛታዊ አንድነትና ሉዓላዊነት፥ በህዝቧም እኩልነትና አንድነት ላይ በምንም መልኩ በማያወላዳ አቋም ላይ ለሚመሰረት ሀገራዊ ኅብረት ነው:: ይህ የኅብረት ጥያቄ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ከልባቸው ሲያምኑበትና ህዝቡም በጋራ የትብብሩ ሂደት እንቅስቃሴ ዋነኛ ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው - ከሁሉም በላይ ቀዳሚው ሀገርና ሕዝብ ናቸውና::"

<u>ከዴሞ፥ ቅድሚያ ሃገርና ሕዝብ ለማዳን፥ ጥቅምት 2000 ዓ.ም. ልዩ ዕትም፥ የተቀነጨበ</u>

## ትንሿ ትዚሃ ደፈትኝ?

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ነሐሴ 1967 ዓ. ም. በይፋ በታወጀበት ጊዜና በተከተሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያሳደረው የጎላ ተስፋና እምነት ዛሬ ድርጅቱ በህዝቡ ትግል ውስጥ ካለው ድርሻ ጋር ሲነፃፀር አሁንም እንደጎላ ነው ለማለት ያዳግታል:: ይህንን ሁኔታ የተገነዘብን የድርጅቱ አባላት፥ አገራችን ካለችበት ሁኔታ፥ በተለይም ከወቅቱ አገርን ከማዳን ብሄራዊ አጀንዳ አንጻር፥

ከድርጅታችን ብዙ የሚጠበቅበት ወሳኝ ወቅት ላይ መሆናችንን በመገንዘብና ይህንኑ ሁኔታ ለመቀየር ምን ማድረግ እንዳለበት በዝርዝርና በጥሞና በመመርመር መሰረታዊ የሆኑ ውስጠ-ፓርቲ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የውይይት ነጥቦችን በፓርቲው የከፍተኛ አመራር አካል ውስጥ ለመቀስቀስ ተገደድን:: ነገር ግን፥ በፓርቲው አመራር ውስጥ የተነሱትን የውይይት ነጥቦች በቅንነት ተመልክቶና በረጋ መንፈስ ተወያይቶ የጋራ ግንዛቤዎችን ለመጨበጥ ሙሉ ፍላጎትና ፈቃደኝነት አልነበረም::

በአንድ በኩል፥ እስከ ዛሬ ድረስ ተመቻችቶና ተደላድሎ የተቀመጠ አምባገነናዊ የአመራር ቡድን "አልጠየቅም፥ እኛን ለመጠየቅ ማንም የሞራል ብቃት የለውም፥ የውስጣዊ ድርጅታዊ ጥያቄዎች አሁን መነሳት ድርጅቱን ለመበተንና ለወያኔና ለውጭ መንግስቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው..." በሚሉ እብሪተኝነትና የስም ማጥፋት ዘመቻ እንደተለመደው ውይይቱን ለማገድና ለማፈን ከፍተኛ ጥረት አደረገ:: በሌላው በኩል፥ ድርጅቱ ጫጭቶና ወደ ጠርዝ ተገፍቶ ካሁን ቀደም የተነሱት ህዝባዊ ጥያቄዎችና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የድርጅቱ አባላትና የኢትዮጵያ ወጣቶች ውድ ህይወታቸውን የከፈሉባቸው ህዝባዊ ዓላማዎች እውን ሳይሆኑ፥ ድርጅቱን እንደ ግል ንብረታቸው የሚቆጥሩና የሚያዙበት ጥቂት አምባገነኖች ሊያፍኑንና ድርጅቱን እንደፈለጉ ሊያደርጉ መቻል የለባቸውም በማለት ለውጥ ፈላጊዎቹ ባነሷቸው ጥያቄዎችና ባቀረቧቸው የመፍትሄ ሃሳብ አቋማቸው ጸኑ:: ስምምነት ላይ ለመድረስ ግን ጨርሶ አልተቻለም፥ ስለሆነም የአባላት አስቸኳይ ጉባዔ እንዲጠራ ተወሰነ::

ለድርጅቱ መሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ እንዲገኝላቸው የአባላት ጉባዔ ቢጠራም ቅሉ፥ ለውጥ አጋቹና አልጠየቅም ባዩ አምባገነናዊ ቡድን በጉባዔ ዝግጅትና አካሄድ ላይ ጭምር እንቅፋት በመፍጠር ድርጊት ተሰማራ:: ጉባዔውን እንዲያዘጋጅ የተሰየመውን ኮሚቴ ስልጣንና ሀላፊነት በተደጋጋሚ ከመጋፋትና ከመጣስ አልፎ፥ ለጉባዔው መቃናት እንዲረዳ ከተወሰነው የጉባዔው ተሳታፊ አባላት የመመዘኛና የውክልና ደንብ ውጭ በአባልነት የማይታወቁና ጨርሶ ውክልና የሌላቸውን በማምጣት የጉባዔውን ቦታ በማጣበብና በማጨናነቅ በጋራ የተጠራው ጉባዔ እንዲሰናከልም አደረገ:: ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ዴሞክራሲያዊ) የራሱን ጉባዔ በተለየ ስፍራ በማካሄድ ድርጅቱን አጠናክሮና መዋቅራዊ መስተካከሎችን አድርጎ ትግሉን በተሻለ ሁኔታ ለማስቀጠል ችሏል::

## ችግሮቻችንና መፍትሄዎቻችን ምን ነበሩ?

ችግሮቻችን በሁለት ይከፈላሉ:: አንደኛው የድርጅቱን አጠቃላይ የአደረጃጀትና የእንቅስቃሴ ድክመቶችን የሚመለከት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ የድርጅቱን ውስጣዊ የአሰራርና የግንኙነት ዝንፈቶች ላይ የሚያነጣጥር ነው::

አባላት ጠንቅቀው እንደሚያውቁት ድርጅታችን በአገር ቤትና በአካባቢው የጎላ እንቅስቃሴ ለብዙ ዓመታት አለማሳዬቱ የማይታበል ነው:: ይህ ድርጅታዊ ድክመት ደግሞ እጅጉን ጎልቶ የወጣው በምርጫ 97ና ከዚያ በኋላ በተከተሉት ሁኔታዎች ነው:: ድርጅታችን የሚንቀሳቀሰው በህቡዓዊ ስልት ነው ቢባልም፥ በምርጫው ወቅትና ከምርጫው በኋላ የህዝቡን ትግል በተቀናጀ መልኩ የሚያስተባብር ጠፍቶ ህዝቡ "የመሪ

ድርጅት ያለህ" በሚልበት ወቅት ድርጅታችን እንደአንጋፋና የረጅም ዓመታት የትግል ተመክሮ እንዳለው የፖለቲካ ድርጅት የጎላ ድጋፍ ለመስጠት ያለመቻሉና በአቅሙ ለህዝቡ ወቅታዊ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አለመቻሉ የድርጅቱን ሙሉ ይዞታ በገሀድ ያሳየ ነው:: ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የድርጅቱ አባላት ቀደም ብለውም ከዚሁ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ብዙ ጥያቄዎች ደጋግመው አንስተዋል:: እንዲያውም በርከት ያሉቱ "በተግባር ጎልቶ ከማይታይ ድርጅት ጋር ለምን እንታሰራለን?" በማለት ድርጅቱን እየተው መውጣት መጀመራቸው አይካድም:: የነበረው አመራር ግን እነኝህን ድርጅታዊ ችግሮች በመገምገም በቂ ምላሽ ወይም ተፈላጊውን ዓይነት ለውጥ ለማድረግ አልፈለገም÷ የአባላት ጥያቄዎችንም ለመመለስ አልቻለም:: ይልቁንም÷ የድርጅታዊ ችግሮችን መኖር በመካድና የአባላትን ጥያቄዎች በማጣጣል "ለምን እንነካለን" በሚል ትዕቢት ጥያቄዎቹን በሚያነሱ የድርጅቱና የአመራር አባላት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ተከፈተ:: ድርጅቱ አስፈላጊ ለውጦችን በማድረግ እንዳያድግ እንቅፋት መሆን ተመረጠ::

ምርጫ 97ን ተከትለው የመጡት ሁኔታዎች የድርጅታችንን ድክመቶች አጉልተው ቢያወጡም ችግሮቹ ወያኔ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የነበሩ ናቸው:: ይህ ደግሞ ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት የትግል ዕድሜ አንፃር ሲታይ ረጅም ጊዜ ነው:: በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ተጨባጭ ለውጥና እድገት ለማሳዬት ካልተቻለ ደግሞ ችግር አለ ማለት ነው:: ይህ የድርጅቱ ችግር በአገር ቤትና በአጎራባች አገሮች ብቻም የተወሰነ አይደለም:: በምዕራባውያን አገሮችም ውስጥ ባሉት የድርጅቱ መዋቅሮች ውስጥ ጎልቶ የታዬ ነው:: በርካታ የድርጅቱ አባላት በየእለቱ ድርጅቱን ጥለው ሲወጡ እንጂ አዳዲስ አባላት ሲቀላቀሉት አይታይም:: ድርጅቱ ደግሞ በዚህ ሁኔታ ሊቀጥል አይገባም:: እስካሁንም ለመቀጠል የቻለው ታማኝ አባላቱ የየግልና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ጭምር መስዋዕት እያደረጉ ለድርጅቱ በሚከፍሉትና በሚያዋጡት ያላሰለሰ የገንዘብ የቁሳቀስና የጉልበት አስተዋፅኦ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ይህን ድርጅት እስካሁን ተሸክመው ያሉት እነኝሁ ታማኝ አባላት ከመብዛት ይልቅ እየመነመኑ ሲሄዱ ደግሞ ድርጅቱ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድሞ ለመገመት አያዳግትም::

በሌላ በኩል የድርጅቱ ውስጣዊ የአሰራርና የግንኙነት ችግሮች ከዕለት ዕለት መሻሻል ሲገባቸው ይበልጥ እየከረሩ የድርጅቱን መታወቂያ በጎ ባሕርያት ጭምር እያከሰሱ መጥተዋል:: በተለይም በዚህ ረገድ በዋናነት የሚጠቀሱት በመብትና በእኩልነት÷ በግልጥ አሰራርና በተጠያቂነት ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው:: በድርጅቱ ውስጥ ረዘም ላለ ወቅት በመሪነት የቆዩና ይህንንም የረጅም ጊዜ የመሪነት ዕድል በመጠቀም ድርጅቱን የጥቂት ግለሰቦችና የቡድን ብሎም እንደቤተሰብ ንብረት የሚቆጥሩ ጥቂት አምባገነን ግለሰቦች አሉ:: ይህ በድርጅቱ ውስጥ የረጅም ጊዜ የስልጣን ቆይታ በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ መንገዶች ለኒህ ጥቂት አምባገነን ግለሰቦች ልዩ ሀይልና ስልጣን ሰጥቷቸዋል:: ስለዚህም÷ የድርጅቱን አጠቃላይ ይዞታ ይሁን ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚገልጡ መረጃዎች በዚህ የጥቂቶቹ ክበብ በሞኖፖል ተይዟል:: ለበርካታው የአመራሩ አባላት ዜናና መረጃዎች እኩል አይቀርቡም:: ይህ በአመራር አባላት መሀል የሚታየው የዜናና የመረጃ መበላለጥ አግባብ የሌለው የሀይል መዛባትን ከማስከተሉም ሌላ ሁሉም እኩል እውቀት ኖሯቸው ለድርጅታቸው እድገት እኩል አስተዋፅዖ ሊያበረከቱ እንዳይችሉ እንቅፋት ፈጥሯል:: ከዚህም በላይ አሰራርን በመጣስና የአመራር አባለትን በመናቅ የተለያዩ የአመራር ኮሚቴዎች ምድብ ስራዎች ውስጥ ጣልቃ መግባትና ማዳከም በተደጋጋሚ ተከስቷል::

## ችግሮቹን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ነበሩ?

በድርጅቱ ውስጥ ድክመቶችና ችግሮች አሉ ብለው ሀሳባቸውን ያቀረቡ ለውጥ ፈላጊ የአመራር አባላት በአጭርና በረጅም ጊዜ መፍትሄነት ሊዘረዘሩ የሚችሉ በርካታ ሀሳቦችን አቅርበው ነበር። የተሰጡት የመፍትሄ አስተያየቶች ምን ቢደረግ በአመራር አባላት መካከል ቀና ግንኙነት ተፈጥሮ የሚጠበቅባቸውን ግዳጅ ለመወጣት እንደሚችሉና አባላትም የትግል ሞራላቸው ታድሶ የተጠናከሩ ድርጅታዊ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት እንደሚበቁ ግምት ውስጥ ያስገቡ ሀሳቦች ነበሩ። እነኝህንም የድርጅቱ መሰረታዊ ችግሮችና የመፍትሄ ሀሳቦች በየፈርጅ ፈርጃቸው አስቀምጦ ለውይይት የሚያቀርብ አንድ አጠናቃሪ ቡድንም ተመስርቶ ነበር።

### *የአጭር ጊዜ መፍትሄዎች፡-*

1. በአሠራርና ግንኙነት ረገድ ለተነሱት ችግሮች ያሉትን የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ አሠራሮች ማክበር፥ ካስፈለገም የአሠራር ለውጦችንና መሻሻሎችን ማድረግ፥ ከሌሉም የአባላትን መብትና እኩልነት የሚያረጋግጡ አዲስ ዴሞክራሲያዊ የአሠራር ደንቦችን መቅረጽና በተግባር ላይ ማዋል፥
2. በጣም ከተማከለ አሠራር መራቅ፥ በአባላት ሥራና ኃላፊነቶች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፤ ኮሚቴዎችን ገምግሞ እንደገና ማዋቀር፥ የኮሚቴዎችንና ንዑስ ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ እንደገና መመርመር፥ ከምናደርገው ድርጅታዊ ግምገማ ተነስተን ማሻሻያዎችን ማድረግ፥
3. ልዩነቶችንና አዳዲስ ሃሳቦችን አቻችሎ ለማስተናገድ የሚያስችል የውይይትና የቅራኔ መፍቻ ስልት መፍጠር፥ በአካላትና በአባላት መካከል ያለውን የግንዛቤና የልምድ፥ እንዲሁም የመረጃ ልዩነቶችን ለማጥፋት ሰፊና ጥልቅ ውይይቶችን በየጊዜው ማካሄድ፥ የአመራሩን ሙሉ ስብሰባ (ፕሌነም) በፍጥነት መጥራት የሚሉ ይገኙባቸዋል።

### *የረጅም ጊዜ መፍትሄዎች፡-*

በዋነኛነት የቀረበው የረጅም ጊዜ መፍትሄ ትኩረቱ የፓርቲው አመራር መኖር ስለሚኖርበት ቦታ ነው። ከሰሜን አሜሪካ፥ ከአውሮፓና ከኤሺያና ሆኖ በአገር ቤትና በአካባቢው ያለውን ድርጅታዊ ሥራና ትግል በበቂና በትክክል ለመምራት ስለማይቻል ከግማሽ በላይ የአመራር አባላት ሙሉ በሙሉ ሙያተኛ ሆነው በሀገር ቤትና በአካባቢው በመሆን ትግሉን የሚመሩበትን መንገድ መሻት፤ በውጪ የሚገኙትም የአመራር አባላት አብዛኞቹን ሙሉ በሙሉ ሙያተኛ ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ ስለመቀየስ የሚመለከት ነበር። ፓርቲውን ስደተኛ ድርጅት ለማድረግ ካልተፈለገ በስተቀር መሰረታዊ የድርጅት አመራር ቦታና ስምሪት ላይ ስምምነት ተደርሶ አጋዥ የሆኑ ሌሎች የለውጥ እርምጃዎችን አከታትሎ ለመውሰድ እንደሚቻልም በርካታ ሀሳቦች ቀርበዋል። ለምሳሌም፥

1. በጎረቤት ሃገሮችና በሃገር ቤት ውስጥ ባሉ አባላት መካከል ጠንካራ ድርጅታዊ ግንኙነት መፍጠር፥ የሃገር ቤቱን ትግል ማጠናከር እንዲቻል ሌሎች ሃላፊነቶችን የማይይዝ ራሱን የቻለ አካል እንዲቋቋም ማድረግ፥

2. የድርጅቱን መዋቅራዊ መሻሻል ማድረግ፥ ጠንከር ያለና ቀልጣፋ ውሳኔን ሊሰጥ የሚችል አካል፥ ለምሳሌ ፖሊት ቢሮ፥ መፍጠር፥
3. የቀድሞ አባላትን በሀገርቤት፣ በጎረቤት ሀገርና በውጭ ሀገርም መልሶ ለማሰባሰብ ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ፥
4. የድርጅት መረጃ ልውውጦች ወይም ሚስጥራዊ ዜናዎች ሁሉም የአመራር አባላት ማወቅ ያለባቸውን እንዲያውቁ ለማድረግ እንዲቻል በተጨባጭ መመዘኛ ደንብ ማውጣት፥
5. የአመራር አባላት በየቦታው ተንቀሳቅሰው ድርጅታዊ ሥራዎችን እንዲሠሩ ለማድረግና ሥራዎችን ለማቀላጠፍ እንዲቻል የድርጅቱ የገንዘብ ችግር የሚፈታበትን መንገድ ማጥናትና በዚህ ረገድ ሊጠቀሙ የሚችሉ አባላትንና ደጋፊዎችን መፈለግ ፥
6. በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ድርጅታዊ አካላትና መዋቅሮች እራሳቸውን በራሳቸው የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን እንዲያካሂዱ ሥልጣን ያላቸው የድርጅቱን ማዕከሎች መክፈት የሚሉ ይገኙባቸዋል።

አስገራሚው ነገር አምባገነናዊው ቡድን በእነኝህ የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ አልነጋገርም አለ። የአመራር አባላት አንዋደድም፥ አብረን ልንሰራ አንችልም፥ ስለዚህ የአባላት ጉባዔ ይጠራልኝ ብሎ ወሰነ። ጥቂት የዚህን ጉባዔ መጠራት የተቃወሙ የአመራሩ አባላት ቢኖሩም፥ ጉባዔው ይጠራ ብሎ ሀሳቡን ያቀረበው የአምባገነኑ ቡድን ያሰማው ምሬትና ያሳየው ማካረር ከጉባዔ ውጭ ለየትኛውም የመፍትሄ መንገድ አማራጭ የማይሰጥ ነበር። ስለዚህ፥ አብዛኛው የአመራሩ አባለት በጉባዔ መጠራት ተስማሙ። ይሁን እንጂ የጉባዔው ዝግጅትና አካሄድ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ገጠሙት፥ በድርጅቱ ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ መልኩ ግልፅ ማጭበርበርና "ካልፈለጋችሁ በሩ ያውላችሁ" የሚሉ አስፀያፊ ቃላት ሳይቀሩ ተደመጡ። በአባላት ሙሉ ፈቃድና ፍላጎት የተመረጡ የአመራር አባላትም "...ሁሉም ታማኝ ናቸው ማለት አይደለም..." ተባለ። ለለውጥ የተነሱ የድርጅት አባላት በጠላትነት ተፈርጀው በጥሪ ከተገኙበት አዳራሽ ለቅቀው እንዲወጡ ከፍተኛ ግፊት ተደረገ - ዛሬ ያለንበት ሁኔታ ላይም ተደረሰ።


**ለምትፅፉልን ወይም ለምትደውሉልን አድራሻችን**

**EPRP (Democratic)**
**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Silver Spring MD 20877**

**EPRP (Democratic)**
**P. O .Box 88675**
**Los Angeles CA 90009**

**EPRP (Democratic)**
**P. O. Box 8141**
**Silver Spring MD 20910**

**E Mail To EPRP@aol.com**
**Telephone:- 301-587-4466**
**301-587-4465**
**Fax: 202-449-8363**